# መጸለይ ለምን አስፈለገን?

## (Why Should We Pray?)

***በሆሊ ኤል. ሙዲ (Hollie L. Moody)***

www.DivineRevelations.info

የሚከተለውን ነገር ያየሁት በጥር 28 2000 ኢ.ም (እ. ኤ. አ)/ 08:15 PM/ ነው። ሆሊ ኤል. ሙዲ



ጌታን በግዙፍ ነጭ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት። በፊቱ ሰዎች በረዥም ሰልፍ ተሰብስበው ነበር። እነዚህ ሁሉ ሰዎች ፊት ስላልነበራቸው ግራ ተጋብቼ ነበር። ፊታቸው በሚኖርበት ቦታ ላይ ምንም ነገር የለም፥ ባዶ ነው።

እያንዳንዱ ሰው በጌታ ፊት በሚቀርብበት ጊዜ፤ መጽሐፍ ይከፍትና ያ ሰው ያደረገውን ነገር ሁሉ ከዛ ላይ ያነባል። ሁሉ ነገር እዛ ላይ ሰፍሯል (ተጽፏል)፥ እና ጌታም መጽሐፉን ሙሉ ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ ያነባል። በዚህ አንድ መስመር ላይ እያንዳንዱ ሰው ፍርድ እየተሰጠው ነበር እናም ፍርዱም ወደ ሲኦል እንዲወርዱ ነበር። ጌታም ወደ ሲኦል እንዲሄዱ ለእያንዳንዳቸው በተናገረ ቁጥር፥ የተነገረው ሰውዬ መጮህ፣ እና ማልቀስ፣ እና ጌታን አንድ የመጨረሻ እድል እንዲሰጠው መማጸን ይጀምራል። ጌታም በጉንጮቹ ላይ የእንባ ዘለላዎች ይወርዳሉ፥ ነገር ግን እራሱን ይነቀንቅና ንስሃ ለመግባትና ለእርሱ ለመኖር በጣም ብዙ እድል እንደነበራቸው ለእያንዳንዱ ሰው ይነግር ነበር። ይሄም ለተወሰነ ረዘም ላል ጊዜ ቀጥሎ ነበር።





በመጨረሻም ጌታ ወደ እኔ ተመለከተነና ***"ለምንድን ነው ዝም ብለሽ የቆምሽው?"*** በማለት ጠየቀኝ። በጣም ግራ ተጋባሁ። ***"ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ ጌታ ሆይ?"*** በማለት መለስኩለት። ጌታም **"ጸልዪ"** ብሎ መለሰልኝ። ስለዚህም መጸለይ ጀመርኩ ነገር ግን በትጋት አልነበረም የምጸልየው። ከጥቂት ሰዓት በኋላ ጌታ ወደ እኔ ዞረና በሚያሳስብ ሁኔታ **"እነዚህን ሰዎች ተመልከቺያቸው። በደንብ ተመልከቺያቸው።"** አለኝ። ልክ ስመለከታቸው ፊታቸው መታየት ጀመረ። በሩቅ የማውቃቸው ሰዎች ሆነው ተገኙ። የሩቅ ሰዎች ነበሩ። ቀጥሎ ትንሽ ጠንከር አድርጌ መጸለይ ጀመርኩ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ጌታ በድጋሚ ወደ እኔ ዞረና ኮስተር ባለ አትኩሮት እንዲህ አለኝ፣ **"እነዚህን ሰዎች በድጋሚ ተመልከቺያቸው።"** አሁን ሰዎቹ ጓደኞቼ ሆነው ተገኙ። **"በደንብ መጸለይ አለብሽ"** ብሎ ጌታ ገሰጸኝ። ቀጥሎ በደንብ ጠንከር አድርጌ መጸለይ ጀመርኩ። ነገር ግን አሁንም በረዥሙ የተሰለፉት ሰዎች ወደ ጌታ ፊት ይቀርባሉ፣ ጌታም የሕይወት ታሪካቸውን ከራሳቸው የግል መጽሐፍ ላይ ያነብላቸውና ከዛም ይፈረድባቸዋል።

አሁንም በድጋሚ ጌታ ወደ እኔ ዞረ፤ ነገር ግን አሁን በቁጣ ነበር። እየተፈረደባቸው በነበሩ ነፍሶች አሁንም እያለቀሰ ነበር። **"እዚህ ጋር እየተከናወነ ያለውን ነገር እየተረዳሽና እያስተዋልሽ ነው?"** ብሎ ጌታ ጠየቀኝ። ቀጥሎም **"እነሆ!!"** አለ። ከዛም አንድ ጉድጓድ በረዥሙ ከተሰለፉት ሰዎች በስተ ኋላ ተከፈተ። ወደ ቀዳዳው በቀስታ ተመለከትኩኝ። ከውስጡ አሰቃቂ የሆነ ጨለማ ይወጣ ነበር። ጩኸት፣ ኡኡታ፣ ለቅሶና ማቃሰት ከቀዳዳው ውስጥ ሲወጣ እሰማ ነበር። **"ሂጂና ተመልከቺ"** ብሎ ጌታ አዘዘኝ። ማየት አልፈለኩም ነበር። በጣም ፈርቼ ነበር ነገር ግን ልክ የሆነ እጅ በጀርባዬ ላይ ወደዚህ ጥቁር ጉድጓድ ሲገፋኝ ይሰማኝ ነበር።



ወደዚህ ጥቁር ጉድጓድ ጫፍ ስደርስ፥ ውስጡን ወደ ታች ተመለከትኩኝ። ከዛም በፍርሃትና  በታላቅ ድንጋጤ ወደ ኋላ ተመለስኩ።ጥቁር ጉድጓዱን ወደ ታች ማየት እችል ነበር። በጣም ረዥም ቁልቁለታማ ዋሻ ይመስል ነበር። የሚጨሱና የሚንተከተኩ ብዛት ያላቸውን ሰዎች በጉድጓዱ መጨረሻ ማየት እችል ነበር። እርስ በእርስ ጭንቅንቅ ብለው ነበር፥ በመካከላቸው ምንም አይነት ክፍተት አልነበረም። የእሳት ነበልባልና ቀይና ብርትኳናማ ቀለም ያለው መብራት ከዚህ ጥቁር ጉድጓድ መጨረሻ ይወጣ ነበር። የሰልፈር (sulfur) ሽታ ሸተተኝ። እሳትና የእሳት ነበልባል አይቼ ነበር። የእሳቱ ሀይለኛ ግለት ይሰማኝ ነበር። በዚህ ጥቁር ጉድጓድ መጨረሻ ትሎች በሰዎቹ መላ ሰውነት (አካል) ላይ ሲርመሰመሱ ተመለከትኩ። ሰዎቹ በእሳት ውስጥ ነበሩ ነገር ግን በእሳቱ ተቃጥለው አይጠፉም ነበር። ነገር ግን ከእሳቱ የተነሳ በስቃይና በህመም ይጮኹ ነበር። ወደ ላይ ወደ ጥቁሩ ጉድጓድ አፍ ይመለከቱ ነበር። እጃቸውና ክንዳቸው ወደ ላይ ተዘርግተው ነበር። ልክ እንደ ትልቅ ማዕበል ያለእረፍት ወደዚያና ወደዚህ ይንቀሳቀሱ ነበር። እናም ነፃ ለመውጣትና ምህረት ለማግኘት ይጮኹ ነበር። ነገር ግን ምንም አይነት ምህረት የለም። ምንም ነፃ መውጣት የለም።

በፍርሃት፣ በታላቅ ድንጋጤና ተስፋ በመቁረጥ ከጉድጓዱ ጫፍ ወደ ኋላ ተመለስኩ። ወደ በስተኋላ ጌታ በዙፋኑ ላይ በተቀመጠበት አቅጣጫ በኩል ዞርኩኝ። አሁንም ድረስ ከመጽሐፉ ላይ እያነበበ ነበር። አሁን በጣም ትላልቅ፣ መጨረሻ የሌላቸው መጽሐፍት ከዙፋኑ ቀጥሎ ተከምረው ተመለከትኩኝ። እያንዳንዱ እነዛ መጽሐፍት ላይ የተጻፉ ሰዎች ገና እንደሚፈረድባቸው ተገነዘብኩኝ። በጌታ ፊት የተሰበሰቡትን፥ በረዥም መጨረሻ በሌለው ሰልፍ ተሰልፈው ፍርድ የሚጠብቁትን ሰዎች አየኋቸው። አሁን የሁሉንም ፊት በደንብ ማየት እችል ነበር። እነሱም ጓደኞቼ፣ ቤተሰቦቼ፣ ዘመዶቼ ነበሩ። እናም እየተፈረደባቸው ነበር። ከዛም ወደ ጥቁሩ ጉድጓድ ሲጣሉ ተመለከትኳቸው፤ እናም ወደ ረዥሙ ዋሻ ወደ ታች በመወርወር ላይ ሳሉ በጣም ሲጮሁ ሰምቼአቸው ነበር።

ጌታም በጉንጮቹ ላይ ዕንባ እየተዥጎደጎደ ወደ እኔ ዞረና **"አሁን ጸልዩ"** አለኝ። ለነዚህ ሰዎች ምህረት እንዲደረግ ወደ እግዚአብሔር ማልቀስና መጮኽ ጀመርኩኝ። እያንዳንዱ ሰው ሲፈረድበት ወደ ጥቁሩ ጉድጓድ ጫፍ በሩጫ እሄድና ከጥቁሩ ጉድጓድ ስቤ ለመመለስ እሞክር ነበር። እጃቸውንና ክንዳቸውን እይዝና ከዛም እንዳያመልጡኝ ስሞክር ነበር። ነገር ግን ከእጆቼ ያመልጡኝ ነበር። የምወዳቸው ሰዎች ወደ ጥቁሩ ጉድጓድ እንዳይገቡ የተቻለኝን ነገር ሁሉ ለማድረግ በብቸኝነት ስጣጣር ነበር። ተንጠራራውና ጌታን ያዝኩት ከዛም ሌላኛውን እጄን ወደ ጥቁሩ ጉድጓድ ሰድጄ ሰዎችን ለመያዝና ከጥቁሩ ጉድጓድ ለማውጣት ሞከርኩኝ።

**"ልቀቂ"** ብሎ ጌታ ነገረኝ። ***"አንተን ከለቀኩህ እኔም ወደ ጉድጓዱ መግባቴ ነው።"*** ብዬ ተቃወምኩ። ጌታም በድጋሚ **"ልቀቂ"** አለኝ። ከዛም ለቀኩት። የማይታዩ እጆች ይዘውኝ የነበሩ ነበር የሚመስለው። በጥቁሩ ጉድጓድ ጫፍ አጠገብ ተኛሁኝና እጄን ወደ ታች ሰድጄ ወደ ጥቁሩ ጉድጓድ የሚወርዱትን ሰዎች ለመያዝና  ለመጎተት ሞከርኩኝ። እኔ እራሱ በነበልባሉና  በእሳቱ በመቃጠል ላይ እንዳለሁ ተሰማኝ። አልፎ አልፎ የሆነ ጥፍር ከጥቁሩ ጉድጓድ ወጥቶ ሲመታኝ ተሰምቶኝ ነበር። ክንዴ ላይ የመቃጠል ስሜት ተሰምቶኝ ነበር ከዛም የመቧጨር ምልክት ክንዴ ላይ ተመለከትኩኝ።



የምወዳቸው ሰዎች ነጻ እንዲወጡ ወደ እግዚአብሔር በማልቀስና በመጮኽ ላይ ነበርኩኝ። በምወዳቸው ሰዎች ላይ ምህረት እንዲደረግና ወደ ጥቁሩ ጉድጓድ እንዲወርዱ እንዳይፈርድባቸው እግዚአብሔርን እየተማጸንኩት ነበር። ጌታም **"የአንቺ ለሆኑትና ለጠፉት ለምትወጂአቸው መጸለይ ቀላል ነው።"** አለኝ። **"አስታውሺ፥ ሁሉም የጠፉት እኔ የምወዳቸው ናቸው። ለጠፉት ልጆቼ ልክ አሁን አንቺ እየጸለይሽ እንዳለሽው የእኔ ልጆች መጸለይ እንዲጀምሩ እፈልጋለሁ። ለጠፉት ልጆቼ በመካከል ባለው ክፍተት የሚቆሙና የሚያማልዱ ትውልድን አስነሳለሁ። እነዚህ አማላጆች የጦርነቱን እሳት ይቀምሱታል፥ በእርሱም ይቃጠላሉ። የሲዖል ሀይላት በእነርሱ ላይ ይወጡና ያጠቋቸዋል። ነገር ግን እኔ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ እይዛቸውማለሁ። አሁንስ ትጸልዪአለሽ?"**

## --ሆሊ ኤል. ሙዲ

**በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ ጌታ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።**

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ቢኒያም ጌታቸው። Translated to Amharic by Biniyam Getachew, bgmanoftheyear@gmail.com